የሰበር መ/ቁ/ 32414

ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ መድሕን ኪሮስ

አቶ ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ - ከጠበቃ ዳኛቸው ተስፋዬ ጋር ቀረበች

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሃሳብ ከፋይ ጌራወርቅ ቀረበች፡፡

2. ደረጀ ጌራወርቅ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በተጀመረበት በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁንዋ አመልካች ሚች አቶ ጌራወርቅ ሀሩይ (ባለቤትዋ) አድርገውት ያለፉት ኑዛዜ መሠረት ተደርጐ የወራሽነት ማስረጃ ይሰጣት ዘንድ በመጠየቅዋ ፍ/ቤቱም ጥያቄዋን በመቀጠል የኑዛዜ ወራሽነት በማለት ማስረጃውን ሰጥቶአት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ማስረጃው መሰጠት አልነበረበትም በማለት መቃወሚያ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ጉዳዮን በድጋሚ ያየ ሲሆን በመጨረሻም ሚች አድርገውታል የተባለውን ኑዛዜ ከፊሉን በመሻር የተወሰነውን ክፍሉን ደግሞ በማጽደቅ ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ከአሁንዋ አመልካች ይግባኝ የቀረበላቸው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም



ውሳኔው ጉድለት የለውም ብለዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እደተመለከተው ክርክሩ ሊነሳ የቻለው ሚች አደረገው የተባለው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል የሚል ክስ በመቅረቡ ሳይሆን (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 973) ኑዛዜውን መሠረት በማድረግ የወራሽነት ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ይሰጠኝ (የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1)) በማለት አመልካች ጥያቄ በማቅረብዋ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርበው ክስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ከሚቀርበው ጥያቄ (አቤቱታ) የተለየ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ በመሆናቸውም የተለያየ ውጤት ነው ያላቸው፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) እንደተደነገገው ወራሽነኝ የሚል ማንኛውም ሰው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጠው ዘንድ ለፍ/ቤት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከመቀበሉ በፊት ጠያቂው ማስረጃዎቹን ሁሉ እንዲያቀርብ በማድረግ እና አስፈላጊ መስሎ የታየውን ዋስትና እንዲሰጥ በማስገደድ ጭምር ዋስትናውን ካገኘ በኋላ የተጠየቀውን የምስክር ወረቀት ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(2) ተመልክቶአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቱ የአመልካቹን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ሰጥቶት የነበረውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰርዘው እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) የተቀመጠው ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ እንደሚቻለው የምስክር ወረቀቱ በጠያቂው አቤቱታ መነሻነት የሚሰጥ ቢሆንም የተሰጠው ያለአግባብ ነው

የሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩንና መቃወሚያው ተገቢ ሆኖ ከተገኘም የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝ መሆኑን ነው፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት ጥያቄውን ተቀብሎ የምስክር ወረቀቱን ሰጥቶ እንደነበር እንመለከታለን፡፡ ይህም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 996(1) የተመለከተውን ድንጋጌ ተከትሎ የተፈጸመ በመሆኑ ትክክል ነው፡፡ ሌላው ቀጥለን የምናየው ተጠሪዎች የተሰጠውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት በመቃወም መቅረባቸው ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ለምስክር ወረቀቱ መስጠት መሠረት የሆነውን ኑዛዜ ይዘት እና ሕጋዊነትን መርምሮአል፡፡ በመጨረሻም ኑዛዜውን በከፊል በመሻር በከፊል ደግሞ አጽድቁአለሁ ብሎአል፡፡ በበኩላችን ትክክለኛ አካሄድ ሆኖ ያላገኘነውም ይህንን ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ በሕጉ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ኑዛዜው ፈራሽ ነው እንዲባል ክስ አልቀረበለትም፡፡ የፍ/ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን የተወሰነ በመሆኑ በሥልጣን ክልሉ ስር የሚወድቀውን የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ነው ጥያቄ የቀረበለት፡፡ ይህን ጥያቄ ተቀብሎ ሰጥቶት የነበረውን የምስክር ወረቀት ተጠሪዎች ካቀረቡለት መቃወሚያ አንጻር ሲመዝነው ተገቢ አልነበረም የሚል ድምዳሜ ከደረሰም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 998(1) በተደነገገው መሠረት መሠረዝ ነው የነበረበት፡፡ ከዚህ አልፎ ኑዛዜው ፈራሽ ይባል የሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ሊደረግ እንደሚችለው ሁሉ ኑዛዜውን በከፊል ሽሬአለሁ ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡ የሕግ መሠረትም የለውም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ወደ ኑዛዜው ይዘት እና ሕጋዊነት ሁኔታ ገብቶ ውሳኔ መስጠት የሚችልበት ሕጋዊ መንገድ አልነበረውም እንጂ ሕጋዊ መንገድ ነበረው ተብሎ ቢሆን ኖሮ እንኳን የደረሰበት መደምደሚያ የኑዛዜን ፎርም እና ማስረጃ ከሚመለከተው ሕግ አንፃር ሊታይ ፍጹም የተሳሳተ ነው፡፡



ለክርክሩ መነሻ የሆነው ኑዛዜ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ እንደሆነ በፍ/ቤቱ ውሳኔ ተመልክቶአል፡፡ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ሊያሟላቸው የሚገቡትን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች ያሟላ እንደሆነም ፍ/ቤቱ ማረጋገጡን በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ይህን ሁሉ ካረጋገጠ በኋላ በከፊል ሽሬዋለሁ ያለው ሟች ንብረቱ ባልሆነው ንብረት ላይ ጭምር ተናዟል በማለት እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሕጉ በግልጽ እንደተመለከተው በግልጽ የተደረገው ኑዛዜ በሕጉ መሠረት አልተደረገም ተብሎ ሊነቀፍ የሚችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ኑዛዜውን ለመንቀፍ ምክንያት ያደገው ነጥብ የኑዛዜውን ሕጋዊነት በተመለከተ አግባብነት የለውም፡፡ ተናዛዡ የእሱ ባልሆነው ንብረት ጭምር ተናዟል የሚባል ቢሆን የንብረት ክርክር ሲቀርብ እራሱን ችሎ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ነጥብ በማድረግ የኑዛዜውን ሕጋዊነት (ፎርም) መንቀፍ ተገቢ አይደለም የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪዎችን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር የድሬዳዋ ከተማ የመጀመያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 00113/97 የካቲት 30 ቀን 99 ዓ.ም ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 106/99 ግንቦት 8 ቀን 99 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ቀደም ሲል ለአመልካች የተሰጠው የወራሽነት የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡